እርሱን አምነውና ተቀብለው ልጆቹ ለሆኑት የሚራራ፤ በፈተናቸው ሁሉ የሚሸከማቸው፤ የሕመማቸው፣ የብቸኝነታቸውና የምሬታቸውን እንባ የሚያብስ፤ የማይተዋቸው አጥብቆም የሚይዛቸው፤ የሚጠብቅ አባትና የሚመራ እረኛ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ ሕይወቱን የሰጠ ወዳጅና ከሲኦል እሳት የሚያድን አምላክ ነው፡፡ የመንግሥተ-ሰማይን በር ከፍቶ ወደ እግዚአብሔር አብ የሚያደርስ ብቸኛው መንገድ የሆነው ጌታ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ምንጭ ነው፡፡ እርሱ የዘላለም ሰላም፣ ፍቅርና ደስታን ይሰጣል፡፡ ጌታ ኢየሱስ የዓለማት ሁሉ ፈጣሪና አዳኝ አምላክ ሆኖ ሳለ ብዙዎች ቢያገሉትም፣ ብቻውን የሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ ነው! (ዮሐ 1፡1-12፣ ሐሥ 4፡12፣ ዮሐ 3፡16) ይህ ጌታ እንዲህ ይልሃል፤ **"ዛሬ እንድታገኘኝ እፈልጋለሁ!"** ድምፁን እየሰማህ ሳለህ ልብህን አታደንድን! ***"ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው።"***(1ጢሞ 1፡15) ጌታ ኢየሱስን ያገለሉና ያለእርሱ የሞቱት ሁሉ ጠፍተው አሁን በከፍተኛ ስቃይ በሲኦል ይኖራሉ! በመጨረሻም የሙታን ፍርድ በሚሆንበት ጊዜ ፍርዳቸውን ተቀብለው በዲን ወደሚቃጠለው እሳት ባህር ለዘላለም ይጣላሉ! ይህም ሁለተኛ ሞታቸው ነው፡፡ (ራዕ 20፡11-15)

## በቅርቡ ሊከሰት ያለው

⇒ **ንጥቀት:** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመንና ዕለት ዕለት በፅድቅና በቅድስና የሚመላለሱት ሙሽሮች ብቻ መለኮታዊ በሆነ አኳኋን እርሱን በአየር ላይ ለመገናኘት የሚወሰዱበት ክስተት ነው፡፡ በዚህ እጅግ አስደናቂና ሊያመልጥህ በማይገባው ክስተት ላይ የሚሳተፉት ሙሽሮች፣ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል(መጽሐፍ ቅዱስን) የሚከተሉ ናቸው፡፡ በንጥቀት ዕለት ጌታ ኢየሱስ በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምፅና በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ከሰማይ ይወርዳል፤ ወዲያውም በቅፅበተ-ዐይን የምርጦቹ(የሙሽሮቹ) አካል በድንገት ወደ ከበረ ሰማያዊ አካል ይለወጣል፡፡ ጌታን በሰማይ በአየር ተገናኝተው አብረው ወደ መንግሥተ-ሰማይ ይነጠቃሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በመላው ዓለም በተለያዩ ሥፍራዎች የእነዚህ ሰዎች መጥፋት በይፋ ይታወቃል፡፡ (1ተሰ 4፡16-17፣ ማቴ 25፡1-12፣ ማቴ 24፡37-41)



ይህች በራሪ ወረቀት ከኢየሱስ ለአንተ የተላከች የንጥቀት ግብዣ ናት፡፡

- ይህን ቁሳዊ ዓለም የሚወዱና ከኃጢአታቸው ያልተለዩ ክርስቲያኖች እና ንስሃ ገብተው ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው ያልተቀበሉት ሁሉ ለታላቁ መከራ በዚህ ምድር ላይ ይቀራሉ፡፡ ***"በዚያም ወራት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ አያገኙትምም፥ ሊሞቱም ይመኛሉ ሞትም ከእነርሱ ይሸሻል።"*** (ራዕ 9፡6፣ ገላ 5፡19-20፣ ራዕ 3፡1-6)
- ማንም ሰው የንጥቀትን ቀንና ሰዓት አያውቅም፡፡ (ማቴ 25፡13)
- በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ ሁን! የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች ሁሉ ተፈፅመዋል፡፡ ***"እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ።"***(ማቴ 24፡33)

⇒ **ሐሰተኛው ክርስቶስ:** ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን ስለሚገለጠው የዐመፅ ሰው አስጠንቅቆናል፡፡ ውጪው ድንቅና ምግባረ-ሠናይ ሰው ይመስላል፤ ውስጡ ግን እጅግ በጣም ክፉ ነው፡፡ እርሱም፣ "እኔ ክርስቶስ ነኝ" በማለት ዓለምን ሁሉ ያስታል፡፡ ሰዎች ሁሉ፣ "ይህ ሰው በእውነት ክርሰቶስ ነው" ብለው አምነው እንዲከተሉትና እንዲሰቱ፣ የሚሰብክና በእርሱ ፊት ምልክቶችንና ድንቅን የሚያደርግ ሐሰተኛ ነቢይም አብሮት ይገለጣል፡፡ (ራዕ 19፡20፣ ራዕ 16፡13፣ ራዕ 20፡10) ***"ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥ የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። አእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፤ ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነውና፥ ቍጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው።"***(ራዕ 13፡16-18)

ይህ ሐሰተኛ ክርስቶስ ተራ ሰው አይሆንም፤ ነገር ግን ጥበበኛ መሪ ሆኖ አመጣጡ ግን ምድርን እንዲገዛ ኃይልን በሚሰጠው በሰይጣን አሠራር ነው፡፡ (2ተሰ 2፡9-10) በአሁኑ ሰዓት ከመቼውም ጊዜ ይልቅ እርሱ ተገልጦ የሚሠራበት የዓለም ሥርዓት በእጅጉ ተመቻችቶለታል፡፡ ከንጥቀትም በኋላ ተገልጦ፡-

- በሰይጣን ኃይል ምልክቶችንና ድንቅን በማድረግ ዓለምን ያስታል፡፡
- በምድር ላይ ኃጢአት እንዲስፋፋ ሕግ ያወጣል፤ ሰዎችንም ወደ ዘላለማዊ ቅጣት(ሲኦል) ይመራል፡፡
- የአውሬውን ምልክት- 666ን ተግባራዊ ያደርጋል፤ ሰዎችም እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል፡፡



- ሐሰተኛውን ክርስቶስ የሚያመልኩና ምልክቱን የተቀበሉ መጨረሻቸው ሲኦል ነው፡፡ (ራዕ 14፡9-11)
- ሐሰተኛውን ክርስቶስ እንዳትከተለው፤ ወይም እንዳታመልከው! የአውሬውን ምልክት 666ን እንዳትቀበል፡፡




⇒ **የአውሬው ምልክት- 666:** ለብዙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደተገለጠው፣ የአውሬው ምልክት ሰዎች በሐሰተኛው ክርስቶስ ተገድደው በቀኝ እጃቸው ወይም በግንባራቸው የሚቀበሉት ማይክሮ-ቺፕስ(Micro-Chips) ነው፡፡ ይህም ለሰይጣን የመሰጠትና የእርሱ የመሆን ምልክት ነው፡፡ ይህን ምልክት ብትቀበል፣ የማይቀለበስ ነፍስህን ለሰይጣን የመሸጥ ተግባር ነው፡፡ ይኸውም እርሱ አእምሮህን እንዲቆጣጠርና ነፃ ፈቃድህን እንዲወስድ ሕጋዊ መሠረት ይሰጠዋል፡፡ የአውሬውን ምልክት አትቀበል ለዘላለም ወደ ሲኦል ትጠፋለህና! የአውሬውን ምልክት የሚቀበል ምንም ይቅርታ፣ ምንም ድነት፣ ምንም ተስፋ እንዲሁም ወደ መንግሥተ-ሰማይ የመግባት ዳግም ዕድል የለውም! (ራዕ 14፡9-11)




⇒ **ሐሰተኛ ነቢያት፣ ሐሰተኛ ክርስቶሶች፣ ሽንገላና ውሸት:** በመጨረሻዎቹ ቀናት ብዙ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች ይነሳሉ፤ ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርጋሉ። (ማቴ 24፡24፣ ማቴ 7፡15) ሐሰተኛ ነቢያት የበግ ለምድ ስለለበሱ ከውጪ ክርስቲያን ይመስላሉ፤ መልዕክታቸውም

ታማኝነት ያለው እንዲመስል እውነትን ከሽንገላና ከውሸት ጋር ይቀላቅላሉ፡፡

- ሐሰተኛ ነቢያት የጌታን ዳግም ምፅአት ቀንና ሰዓቱን ይናገራሉ፡፡ የጌታን ዳግም ምፅአት ቀንና ሰዓት የሚናገሩትን ማናቸውንም አትከተል፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስህን አንብበህ እውነትን በማወቅ ሐሰትን መለየት መለማመድ አለብህ፡፡

  ***"በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።"*** (ማቴ 24፡23-24፤ ማር 13፡21-23 )

  ***"እንግዲህ እነሆ፥ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፥ አትውጡ፤ እነሆ፥ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ፥ አትመኑ፤ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፡፡"*** (ማቴ 24፡26-27፤ ሉቃ 17፡23-24)

**ሲኦል፡** ከኃጥአታቸው ንስሃ ያልገቡና ጌታ ኢየሱስን ለመቀበል እምቢተኛ የሆኑት ሁሉ የሰይጣን ምርኮኛ ሆነው፣ በጨለማ ውስጥ በማይጠፋ እሳትና የሰው ቋንቋ ሊገልፃቸው በማይችል ልዩ ልዩ ቅጣቶች የሚሰቃዩበት ሥፍራ ነው፡፡ ሲኦል መውጫ የለውም፡፡ (ማር 9፡43-44፣ ኢሳ 66፡24፣ ሉቃ 16፡23-25) ንስሃ ያልገቡ ክርስቲያኖችም ወደዚያው ሥፍራ ይሄዳሉ፡፡ ይህን አስታውስ! በሲኦል ያሉት ለአንድ ደቂቃ ወደ ምድር ተመልሰው ንስሃ ለመግባት ዳግም ዕድል እንዲሰጣቸው እየለመኑ ነው፤ ነገር ግን አይችሉም፡፡ **አንተ ግን አሁን ያ ዕድል አለህና አታባክነው!**

**እሳት ባህር፡** ጌታ የዘላለሙን ፍርድ ሲሰጥ ሐሰተኛው ክርስቶስና ሐሰተኛው ነቢይ፣ በሲኦል ያሉት ሙታን፣ ሰይጣንና መላእክቱ፣ ሞትና ሲኦል ለዘላለም የሚቃጠሉበት የዲን እሳት ባህር ነው፡፡ ይህ የእሳት ባህር ሁለተኛው ሞት ነው፡፡ ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ተፅፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደዚህ እሳት ባህር ይጣላሉ፡፡ (ራዕ 19፡19-20፣ ራዕ 20፡12-15)

**መንግሥተ-ሰማይ፡** ሁሉን ቻዩ አምላክ ለሚወዱትና ቃሉን ለሚጠብቁት ሙሽሮቹ፣ ለዘላለም መኖሪያ ትሆን ዘንድ ያዘጋጃት ውብና ግርማዊት ዓለም ናት፡፡ እግዚአብሔር መንግሥተ-ሰማይን ሲፈጥር ዘላለማዊ ውበትን፣ ክብርን፣ ደስታን፣



አግራሞትንና ምስጢራትን በውስጧ አስቀምጧቸዋል፡፡ በምድር የከበሩ ነገሮች ሁሉ ቢደመሩ፣ በመንግሥተ-ሰማይ ካለው ከአንዲቷም ነገር ጋር እንኳ ሊመጣጠኑ አይችሉም!

## ዛሬ መንግሥተ-ሰማይን ምረጥ!

ወደ መንግሥተ-ሰማይ ሊወስድህ ኃይል ያለው ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ (ዮሐ 14፡6) ማንም በመልካም ሥራው፣ በሥነ-ምግባሩ፣ በራሱ ፈቃድ ወይም ከክርስቶስ ውጪ በሌላ በማመን ወደ መንግሥተ-ሰማይ ሊገባ አይችልም፡፡ በታሪክ ሁሉ ከክርስቶስ በስተቀር ደሙን አፍስሶ በመስቀል ላይ የሞተልህ ማንም የለም፡፡ እርሱ ፈጣሪህ ነው፡፡ ሞትን አሸንፎ ከሞት የተነሣ እርሱ ብቻ ነው! መዳን በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን በእርሱ ብቻ ነው! (ዮሐ 3፡16፣ የሐሥ 4፡12) ***"እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት ሰጠን፤ ይህም ሕይወት ያለው በልጁ ነው፡፡ ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡፡"***(1 ዮሐ 5፡11-12)

ዛሬ መንግሥተ-ሰማይን ምረጥ፡፡ ጌታ ኢየሱስን ከልብህ ተቀበል፡-

- ኃጢአትህን ሁሉ ተናዘዝ ንስሃም ግባ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ወዲያው ይቅር ይልሃል፡፡(1ዮሐ 1፡9)
- ይህን ፀልይ፣ **"ውድ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ጌታዬና አዳኜ አድርጌ ተቀብዬሃለሁ፡፡ አንተ ለኃጢአቴ ሞተህ እንደተነሣህ አምኛለሁ፡፡ ሰይጣንና ዓለምን ክጃለሁ፡፡ እባክህን ስሜን በሕይወት መጽሐፍ ፃፈው፡፡ መንገድህንም አስተምረኝ፡፡ ኃጢአቴን ይቅር ብለኸኝ ስሜን በሕይወት መጽሐፍ ስለፃፍህ አመሰግንሃለሁ፡፡ በጌታ በኢየሱስ ስም! አሜን!"**
- በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር በፀሎት መነጋገር ጀምር፡፡
- በመጽሐፍ ቅዱስ በምታምን እና በመንፈስ ቅዱስ በተሞላች በአቅራቢያህ ባለች ቤተክርስቲያን መሳተፍ ጀምር፡፡
- ሰንበትን ቀድሳት፡፡ በዚህች ቀን ቤተክርስቲያን ሂድ፡፡ እግዚአብሔርን አክብርባት እንጂ የራስህን ምኞት ለማድረግ አትሩጥ፡፡ (ኢሳ 58፡13-14፣ ማቴ 5፡17-20)
- ከዮሐንስ ወንጌል ጀምረህ በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚልህን አድርግ፡፡



# አስተውል!

# የዓለም ፍፃሜ ተቃርቧል!

## ጌታ ኢየሱስን ለመገናኘት ተዘጋጅ!

ዛሬ በዓለም ላይ በርካታ የሕይወት መንገዶች ያሉ ይመስላል፤ እውነታው ግን **ሁለት መንገዶች**- ሕይወት ወይም ሞት፣ **ሁለት ዕጣ-ፈንታዎች**- መንግሥተ-ሰማይ ወይም ሲኦል ነው፡፡ ወደ መንግሥተ-ሰማይ ሊያስገባህ ብቻውን ኃይል ያለው ፈጣሪህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በእያንዳንዱ የሕይወትህ መንገድ ላይ ቆሞ እንዲህ ይልሃል፤ ***"እነሆ በፊትህ የሕይወት መንገድ እና የሞትን መንገድ አኑሬአለሁ፡፡ የሕይወትን መንገድ ምረጥ በሕይወትም ትኖራለህ፡፡"*** (ዘዳ 30፡19) የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት በበራችን ነው! በቅርቡ ሊከሰት ስላለው ነገር ዕወቅ፡፡ ተዘጋጅ!

*መንግሥተ-ሰማይ እና ሲኦል ይጠብቁሃል!*

*ዛሬውኑ የዘላለም መኖሪያህን ምረጥ፡፡* (2ቆሮ 6፡2)

## ስለኃጢአተህ የሞተልህን ጌታ ኢየሱስን ታውቀዋለህን?



እያንዳንዱን ሰው የፈጠረው ኢየሱስ፣ በማህበረሰብ ውስጥ ያለህ ቦታ፣ ዘርህ፣ ፆታህ፣ ወይም የቀደመው ኃጥአትህ ምንም ሳያግደው በጥልቅ ፍቅር ሁሌም ይወድሃል፡፡ (ሮሜ 5፡8፣ ኤፌ 5፡2)